# የመታሰቢያ ዜማና ግጥም

## ስንኝ

ሀሳብ እንደ ንፋስ ፣ ውስጤን እያመሰ
ልቤን አቀለጠ፣ ዝምታን አነገሰ።
ያልተነፈስኩት እሳት፣ በጉሮሮዬ ላይ ቆሞ
ነፍሰን በጥብጦ፣ እረፍት አሳጥቶ።

አንድ ጊዜ ልጄ ብቻ ላቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ ያለውን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣

ልጄ አቢጋሌዬ አቢዬ አቢሹ

አንድ ጊዜ ልጄብቻ ለቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ የደበቅኩትን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣

ጨለመብኝ ቀኑ መውጫው ጠፋኝ መንገዱ፣
መጥፎ ሀሳቦች መጡ እየተራመዱ።

አንዳንዱ ቀን እጅጉን ይረዝማል
ከሰው ተለይቶ ብቻ ያሰቆዝማል
የፀሐዩ ብርሃን ጨልሞ ይታየኛል
ቤቱም እንደ ባዕድ ጭራሹን ያስፈራኛል።

## ስንኝ

በጥያቄ ባህር ነፍሴ ትዋኛለች
መልስ ፍለጋ እጅጉን ትዞራለች
ለምን የሚለው ቃል ደጋግሞ ይጮኻል
የውስጤ እሳት እየነደደ ፋታ ይነሳኛል።

## ስንኝ

እማርራለሁኝ ከራሴው ጋር ሆኜ
ሰላም አጣሁኝ በዝቷል መከራዬ
እጆቼን ዘርግቼ ለምን እላለሁኝ
ምክንያቱን አጥቼ እጨነቃለሁኝ።

አንድ ጊዜ ብቻ ላቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ የደበቅኩትን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣

## ሰንኝ

አምላኬ ሆይ ሰማኝ የልቤን ጩኸት
ውስጤ ተሰባብሯል በከባድ ሐዘን ስሜት
አንድ ልጄን ወሰደህ እቅፌን ስታሰቀረው
ዓለሙ ሁሉ ባዶና ከንቱ ሆኖ ታየኝ ሳሰበው ።

## አዝማች

አቢጋይል፣ ብርሃኔ፣ ደማቅ ኮከቤ፣
በሰማይም ብትሆኚ፣ አለ ሁሌ ከልቤ፣
በእያንዳንዱ እንባ፣ በእያንዳንዱ ምሽት፣
ትመጫለሽ አጠገቤ፣ እያለሁ ብርሃንሽን።

አንድ ጊዜ ብቻ ላቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ የደበቅኩትን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣

አቢጋይል፣ ልቤ ሁልጊዜ እንዲህ ይላል፣
አሁን መልአኬ ሆነሻል፣ መንገድሽን አግኝተሻል፣
ምንም እንኳ ብትለዪኝም፣ አሁንም ትኖሪያለሽ፣
በደስታዬም በህመሜም ውስጥ ሁሌም ትገኛለሽ።

ለምን አምላኬ ለምን አምላኬ
የምወደውን ወሰድክብኝ፣ አንድ ልጄን ነጠቅከኝ
እቆዝማለሁ እማራራለሁ

## ሰንኝ

የሳቁ ድምፅ ዛሬ በቤቴ የለም
የጨዋታው ትዝታ ከውስጤ አይጠፋም
ያፈቀርኩት አንቡጥ ገና ሳይፈካ
ለምን ቀጠፍከው እንዲህም አለ ለካ።

## ሰንኝ

ለካስ መኖር ከባድ ነው እንዲህ ሲሆን
ተሰፋህ ሲቆረጥ፣ ስታጣ የልብህን
በእቅፌ ይዤው ማየት ሰመኝ ኖሬ
ዛሬ ግን ሄደብኝ፣ ቀረሁኝ ብቻዬ።

አንድ ጊዜ ብቻ ላቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ የደበቅኩትን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣

## ሰንኝ

ሰው ይለኛል አይዞህ ሰው ይለኛል በርታ
እኔ ግን አላገኘሁም እረፍት ለአፍታ
ጥያቄዬን ይዤ ካንተ ደጅ ቆሜያለሁ
መልሱን እስክማገኝ ድረስ እጮኻለሁ።

## ድልድይ

ደመናው ከበደኝ፣ ሰማዩ ጠቆረ
የአባትነት ፍቅሬ በሐዘን ታሰረ
ግን ደግሞ አውቃለሁ አንተ አትረሳኝም
ምንም ቢጨልምብኝ ጥለኸኝ አትሄድም።

አንድ ጊዜ ብቻ ላቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ የደበቅኩትን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣

## አዝማች

አቢጋይል፣ ብርሃኔ፣ ደማቅ ኮከቤ፣
በሰማይም ብትሆኚ፣ ሩቅ አይደለሽም ከልቤ፣
በእያንዳንዱ እንባ፣ በእያንዳንዱ ምሽት፣
ድምጽሽ ይሰማኛል፣ በዝምታው ቤት

አቢጋይል፣ ልቤ ሁልጊዜ እንዲህ ይላል፣
አሁን መልአኬ ሆነሻል፣ መንገድሽን አግኝተሻል፣
ምንም እንኳ ብትለዪኝም፣ አሁንም በልቤ ትኖሪያለሽ፣
በደስታዬም በህመሜም ውስጥ ሁሌም ትገኛለሽ።

አንድ ጊዜ ብቻ ላቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ የደበቅኩትን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣

ለምን አምላኬ ለምን አምላኬ
የምወደውን ወሰድክብኝ፣ አንድ ልጄን ነጠቅከኝ
እቆዝማለሁ እማራራለሁ

## መደምደሚያ

የልቤን ስብራት አንተህ ጠግንልኝ
ለዚህ መሪር ጥያቄ እረፍትን ሰጠኝ
በመረጥከው መንገድ መጓዙን ባላውቀው
ለነፍሴ ሰላምህን፣ ለዓይኔ ብርሃንህን ሰጠው

አንድ ጊዜ ብቻ ላቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ የደበቅኩትን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣

## ድልድይ

አንድ ጊዜ ብቻ ላቅፍሽ ብችል ኖሮ፣
በውስጤ የደበቅኩትን ሁሉ በነገርኩሽ ኖሮ፣
ግን አውቃለሁ ከላይ ሆነሽ እንደምትጠብቂኝ፣
በነፋሻማው አየርና በህልሜ ውስጥ እንደምትታዩኝ።

## መውጫ

ስለዚህ እኖራለሁ፣ ስምሽን እየጠራሁ፣
ፍቅርሽን እንደማይጠፋ እሳት ተሸክሜያለሁ፣
እንደገና እስክንገናኝ ድረስ በዚያ ቀን
አቢጋይልዬ አንቺ ነሽ የኔ መዳን።

---

**አቢጋይልዬ የዘላለም ጓደኛዬ ልጄ**